# አጉል ቦታ አምሽቼ

ነገደ ጎበዜ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የግጥም ውድድር በፕሬዜንዳንቱ የተሸለምኩበትና ኮሌጅ ደይ የተነበበ

1955 ዓ.ም

*በአለፈው ሰሞን ነው ቅዳሜ ለት ማታ*
*የኔ ልጅ ደግሶ*
*ጓደኞቹን ሆሉ ከየትም ከየትም*
*በሙሉ አግበስብሶ*
*እንደ አባትነቴ እኔም ተጠርቼ*
*ብዙ ጉድ አየሁኝ ብዙ ተመለከትሁ*
*አዳምጡኝ ልጆቼ*
*ገብቼ ቁጭ እንዳልኩ ልጄን ጠራሁና*
*በል እስቲ ፅዋውን ወዲህ አምጣው ልጄ ልሳለመውና...*
*አልኩና ስጀምር ከት ብሎ ሳቀ*
*እኔም ወዲያውኑ መሳሳቴ ገባኝ*
*ህሊናየ አወቀ*
*ወዲያውኑ ልጄም መንከትከቱን ትቶ*
*ፓርቲ ነው ፕርቲ ነው?*
*ብቻ ስሙን እንጃ አላውቀውም ከቶ*
*የሚባል ጠበል ነው አሁን የምንጠጣው ልንገርህ አባባ*
*እዚሁ ቁጭ ብለህ ሁሉንም ተመልከት ወደ ውስጥ አትግባ*
*ፅዋ እሚሉ ነገር የለም እዚህ ቦታ*
*ብዙ ጉድ ታያለህ ይህ ልዩ ነገር ነው አይዞህ ዛሬ ማታ*
*ምንም አልመለስኩም በጣም አፈርኩና*
*"እሺ" ብቻ ብየው ሄደ ከአጠገቤ ቶሎ ተነሳና።*

*ወዲያው እንግዶቹ አንድ በአንድ እያሉ*
*ሴቶች ከወደፊት ወንድ እያስከተሉ*
*ይገቡ ጀመረ ምን ምን የመሰሉ*
*ሰው መግባት ሲጀምር ሲጋበዝ ሲበላ*
*አንዲቷ ልበ ውልቅ እያረገረገች እየሳቀች ገባች*
*የፈረደበትን ወንዱን አስከትላ*
*እኔም አስገርሞኝ የአለባበሷና የአኳሆኗ ነገር*
*ምን ከርፋፋዋ ነች ይች ሴት አሰዳቢ ምን ያለች ባላገር*
*ልቧ የት ሄዶ ነው እንደዚህ አድርጋ ራሷን መርሳቷ*
*ቢጠፋ ቢጠፋ የእናት ኩታ እያለ የአባት ጋቢ እያለ መጣሉ ደረቷ*
*ራቁቷን ሆና አሁን በዚህ በብርድ እንዲህ መመታቷ*

*እንደ በረሃ ጂን ለምን ፀጉሯ ቆመ እረ ለምንድን ነው አለመበጀቱ*
*እባካችሁ ሰዎች ጤና እኮ አይደለችም አብዳለች ልጂቱ*
*ወፍጮስ እንደ ዋለች እረ ለምንድን ነው ቀዋታ መምጣቷ*
*ዱቄቱ እንዳለ ነው ምንም አልተነሳም አልታጠበም ፊቷ*

ልበ ውልቅነቷ መች እዚህ ላይ ቆመ አለ ትልቅ ነገር በጣም የተረሳ
እጅዋን አልታጠበች አፏን አልታጠበች በልታ ስትጨርስ ገበታ ሲነሳ
እከንፈሮቿ ላይ የጎንደር አዋዜ ተለድፎባታል
ደም ሰርቃ የላሰች የመንደር ልክስክስ ውሻ አስመስሏታል
እጅዋም እንዲሁ ነው አልታጠበችውም ጣቷ ተጨማልቋል
ከወገቧም በታች የሁለት ሰው ቦታ አሰፋፍታ ይዛለች
ከጉልበቷም በታች ምንም ነገር የላት እንዲሁ ባዶ ነች
ይህስ የችግር ነው እኔ እንደመሰለኝ የእናቷን ተውሳ
ሳይሆን እኮ አይቀርም- ቀሚሷ መስፋቱ እንዲህ ያለ መሳ
ግን ደሞ የእናቷ እንዲህ አያጥራትም አይመስለኝም ከቶ
ከሰፊው ይሆናል ቁራጭ ጨርቅ ሰጥታው እንዲህ አበላሽቶ
በጨለማ ሰጥቷት በችኮላ አጥልቃ ይሆናል መምጣቷ
ወደዚህ በሩጫ እንዲህ ልቧ ወልቆ እየታየ ባቷ
ሰፊው ግን አጥፍቷል እንዲህ ከማስፋት
ትንሽ ጠበብ አርጎ ትንሽ ከቁመቱ ቢጨምርበት
"አጥታ ነው ቸግሯት ድሃ ነች የላትም" የሚል ማን ነበረ ይቺን እመቤት?
ደሞስ ለምንድን ነው በነጠላ ጫማ እንዲህ መወጣቱ?
ተረከዝዋ እንደሆን የሚሸፈን ነበር ምነው መታየቱ?
ወይ እንደለመደች ረስታው ይሆናል የቀየረች መስሏት
ወይኔ ተዋረደች አፈር ይብላኝ ልጄ ዛሬስ አጋለጣት
ምን ያለች ጎደሎ ከሁሉ የጎዳት
ምነው ባትወጣስ ከእናቷ ጋር ብትቆይ ይኸ ቢቀርባት
ከሁሉ እሚገርመው እሷን ሰው ነች ብሎ እየተጎተተ
የወንዱ መከተል አይ የኛ ሞጋጋ ምን ሃሞት የሌለው በፍፁም የሞተ
ሌሎች እስኪገቡ መጠበቅ አልቻልኩም ወጣሁ ተነስቼ
በዚች በወጣት ልጅ እንደዚህ መታመም ልቤን ተመትቼ።

ወዲያውኑ ልጄን እውጭ አስጠርቼ
ምነው ምን ሆናችሁ? በሽተኛዋን ልጅ መልሷት እቤቷ
ይሰጉ ይሆናል የት ደረሰች ብለው እናትና አባቷ
ወይንም ነገሯት ቀሚሷን ትቀይር ፊቷን ትታጠበው
ጫማዋም ይለወጥ ፀጉሯን ታበጥረው
በእንዲህ ያለ ቦታ በእንዲህ አይነት ምሽት ሴቶች መምጣታቸው
እረ ለምንድን ነው እንዴትስ ዝም አሉ እናት አባታቸው?
ብዙ አልተናገርኩም የልቤን አውጥቼ ከቶ አልሆነልኝም
አሁንም መልሶ አፌን መታኝ ልጄ አላናገረኝም

አስረድቶኝ ሄደ ነገሩን በሙሉ
የቀሚስን መርጠር የእንዲያም መንቧለሉ
የፊቷንም ዱቄት የጫማውን ሁሉ
የአፏም ላይ አዋዜ የጎንደር አይደለም የአውሮፓ ነው አሉ!
አስረዳኝ ደህና አርጎ ከታች እስከ ላይ
እንዲህ ማስፈራሪያ ሆና ስትታይ
ፋሽን ነው ይለኛል እኔ ታዲያ ይኸ ይገባኛል ወይ?

ግን ድሃ አይደለችም በሽታም አልያዛት ገባኝ ብልሃቷ
ዱቄትም ብዙ አላት የሆዷ ሞልቶላት ተርፏታል ለፊቷ
አዋዜውም ቢሆን የመጣው ከአውሮፓ፣ እሷ አልሰራችውም አልደከመችበት
ታዲያ ምን ቸገራት የዛሬ ልጅ እንደሁ አትወቅጥ አታምስ እንደዚህ አድርጋ ብትጫወትበት
ግን እኔ ያልገባኝ ፈንጣጣ አስቸግራን ሲገኝ መድሃኒቷ
ምን ነካት ልጃችን "ክትባት" መጥላቷ?
ይህን ሳሰላስል ብቻየን ቁጭ በየ ከጠርሙሴ ጋራ
ከወደቤት በኩል ውካታ ቢበዛ ተነሳሁ ላጣራ

ገና በሩ ስደርስ ሰው ሁሉ ተሳክሮ አለቅጥ ጠጥቶ
እዚያ ያለ ሁሉ ወጣት ሽማግሌ ወንዱ ሴቱ ሳይቀር ጭራሽ ነፍሱን ስቶ
ግብ ግብ ገጥሟል ጠብ ይዟል አምርሮ፣ ደስታውን ረስቶት ጨዋታውን ትቶ
እኔ የገረመኝ የሴቷ ድፍረት ነው ወንዱን ተያይዛ
ና ውደቅ ና ተነስ ስትለው አየሁኝ ማጅራቱን ይዛ
ወንድ መቸም የዋህ ማምረሯ አልገባውም ወገቧን ጨብጦ
ዝም ብሎ ይስቃል ሴት ስለያዘችው በሃፍረት ተውጦ
አንዳንዱስ እንጃለት ይለምናል መሰል ልቀቂኝ እያለ
አዘናግቶ ሊያመልጥ በመልካም ፈገግታ አይን አይኗን ያያታል መስሎት ያታለለ
መታገሉ ላይቀር መጣላቱ ላይቀር ከወንድ ቢጣላ
ይሻል እኮ ነበር እንደዚህ አድርጎ ከሚዋረድ ኋላ
እግሩን ወዲያ ወዲህ ሙጃሌ እንደያው ከማፈራገጥ
ጥንቱንስ ባይጠጣ ለሴት ፊት ባያሳይ አርፎ ቢቀመጥ
አይሻልም ነበር ከዚህ ሁሉ ማጥ?
ወኔየ ተነሳ እኔም ደሜ ፈላ ኩታየን አውርጃ
ከጠቡ መሃከል ደቂቃ አልቆየሁም ጉብ አልኩበት ሄጄ
ወንድ ወንዱን ጠመድኩት እኔ እኮ ወንድ ነኝ ሴቷን ማን ይነካል
ግን የልቤ ሳይደርስ ልጄ መጥት ያዘኝ አስወጣኝ ከመሃል

ጠቡም ሁሉ ቆመ ሰው ሁሉ ወደኔ ይመለት ጀመር
እንዲህ ያለች ጎበዝ ወንድ ነች እያለ ነፍጠኛ ባላገር
ልጄም ይዞኝ ወጥቶ እቅድሟ ቦታ
አባባ ላስረዳህ ጠብ እኮ አልነበረም ያ ሁሉ ውካታ
ዳንስ የሚሉት ዘፈን የፈረንጅ እስክታ

ነውና እባክህን ገብተህ ቁጭ በልና ተመልከት በእርጋታ።

ገባሁኝ ቁጭ አልኩኝ እዛች እወንበሬ መከረኛ ቦታ
ስንቱን አሳየችኝ በዚች ሰአት እድሜ ይኸው ዛሬ ማታ!
ማድነቅም ጀመርኩኝ ይህ ዳንስ የሚሉትን የፈረንጅ እስክታ!
ተቃቅፈው ደስ ብሏት እያረገረገች እንዲህ በፈገግታ
ካስደገፈች ወዲያ ሁለቱን ጡቶቿን እደረቱ አምጥታ
የለም ማለፊያ ነው እንዲህ አርጎም የለ አየ ጉድ ጨዋታ!
ትከሻውን ይዛው ወገቧን ጨብጦ እያሽኮረመማት
ጨወታ ነው ይላል እኔ መቼ አጣሁት ይህን ሁሉ ብልሃት

ትልቅ ጉድ ፈላ እንጂ እንግዲህ ምን ቀረ አቅፏት ከአቀፈችው
ያለ ሽማግሌ እናቷ ሳትሰማ ያለ ነገር አባት እሷው ጨረሰችው!
ያልታደለች እናት ልጅ አለችኝ ብላ
ያልታደለች እናት እድራለሁ ብላ
ሰርግ ታስባለች ድግስ ታስባለች እቤቷ ቁጭ ብላ
እኔ አየሁት እንጂ እሷ መች ነበረች ጉዳዩ ሲፈፀም ትልቅ ጉድ ሲፈላ!!

አሁንስ ይበቃል ከእንግዲህስ ጉዱን አትስሙት ልጆቼ
እኔስ ብዙ ነበር የተመለከትኩት እግዚአብሄር ይማረኝ
እርሜን ለአንዲት ማታ አጉል ቦታ አምሽቼ!!

ነገደ ጎበዜ
አ.አ.ዩ.ኮ
1955 አ.ም.